## እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ሁለተኛዉ አስር  ቀናት የክረምት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በይበልጥ የሚጠናከሩበትና የዝናቡ ስርጨትም አብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች የሚያደርስ ሲሆን፤ በመጠንም ረገድ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የሚመዘገብበት ጊዜ ነው፡፡


ባለፉት በጁላይ ሁለተኛ አስር ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በሰሜን አጋማሽ፣ በመካከለኛው፡ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የበለጠ ጥንካሬ የነበራቸው ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ወደ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍል ተስፋፍተው ተስተውለዋል፡፡  በተጨማሪም ከነበረው ጠንካራ የሆነ የደመና ክምችት ምክንያት በአንዳንድ የክረምት ዝናብ  ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስ ያህል በኢጃጂ 34.8፣ በአርጆ 32.4፣ በጊንቢ 65.7፣ በማይጨው 33.0፣ በጨዋቃ 31.5፣ በነቀምቴ 55.1፣ በበደሌ 36.0፣ በዝዋይ 33.0፣ በጂንካ 33.8፣ በላሊበላ 32.2፣ በአዲስ አበባ 36.7፣ በማንኩሽ 43.0፣ በደብረ ብርሀን 30.0፣ በባህርዳር 33.3፣  በላሬ 43.9፣  በጋምቤላ 52.0፣ በጎንደር 63.2፣ በአይከል 30.9፣ በከማሺ 53.3፣  በአልጌ 30.5፣ በአምደወርቅ 68.5 እና በአማን 62.8 በሚ.ሜ. ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት ትግራይ፣ አማራ፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ አብዛኛው ኦሮሚያ፣ ድሬዳዋ፣ ሐረሪ፣ አፋር እና ከሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ዞን ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው ዝናብ ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲነጻጸር ትግራይ አማራ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ አብዛኛው ኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ አፋር ድሬዳዋ፣ ሐረሪ፣  እና ከሶማሌ ክልል የጅግጅጋና የሲቲ ዞኖች ከ5-249 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከ2 እስከ 10 ቀናት ያህል አግኝተዋል (ካርታ 1 እና 2 )፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛ ጋር ሲነጻጸር አብዛኛው አማራ፣ ጋምቤላ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብና ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉባቡር፣ ጂማ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሸዋ እንዲሁም  ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፡ ድሬዳዋ፣ ሐረሪ እና ከሶማሌ ክልል የጅግጅጋ ዞን መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛ በታች ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3)፡፡


ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2017 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




## ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# <u>እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>

ባሳለፍነዉ የጁላይ ሁለተኛዉ አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ ሚቲዎሮሎጂካል ክስተቶች በሰሜን አጋማሽ፣ በመካከለኛው፣ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ከነበራቸዉ የተሻለ ጥንካሬ ጋር ተያይዞ የተሻለ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ አልፎ አልፎ ወደ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍልም የተስፋፋ ሲሆን፤ በተጠቀሱት ሥፍራዎች የተገኘዉ ዕርጥበት አስቀድመው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የተለያዩ ሰብሎች እና ለቋሚ ተክሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በመካሄድ ላይ ለሚገኘዉ የወቅቱ የግብርና ሥራ ዕንቅስቃሴ ማለትም ለማሣ ዝግጅት፣ ለዘር እና ለመሳሳሉት የግብርና ተግባራት አመቺና የጎላ ጠቀሜታ እንደነበረዉ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የምስራቅ የሀገሪቱ ክፍል በመጀመሪያ የጁላይ አሥር ቀናት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የነበረዉን የዕርጥበት ዕጥረት በመጠኑም ቢሆን እንደአረገበዉ ይታመናል፡፡ በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ በረዶ ቀላቅሎ የጣለዉ ከባድ ዝናብ፣ ዝናብ አጠር ለሆኑ፣ ዉሃን የማቆር ሥራዎችን ለመከናወን፣ የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት እና የግጦሽ ሣር መሻሻልና ቁጥቋጦ ለማቆጥቆጥ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ምንም እንኳን የደረሰን ሪፖርት ባይኖርም በረዶ ቀላቅሎ የጣለዉ ከባድ ዝናብ በአንዳንድ ሥፍራዎች በእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የተለያዩ ሰብሎች እና ለቋሚ ተክሎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደነበረዉ ይገመታል፡፡ እንዲሁም ተዳፋት በሆኑ ቦታዎች ላይ የአፈር መሸርሸር እና በጎርፍ መጠረግ ሊያስከትል ይችላል (ካርታ 4)፡፡

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2017 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




## እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ

## በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 11-20 ጁላይ 2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን የክረምት ዝናብ በሚያገኙት ዋና ዋና ተፋሰሶች ላይ ያዳረሰ መሆኑ ተስተውሏል። በመሆኑም አብዛኛው የተከዜ፣ የአባይ፣ የባሮአኮቦ እና የኦሞጊቤ፣ ጥቂት የላይኛው አዋሽ እና የላይኛው ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም በጥቂት ኪስ ቦታዎች በሆኑ የላይኛው አፋርደናከል እና የላይኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች የተሻለ እርጥበት የተስተዋለባቸው ናቸው። በሌላ በኩል አብዛኛው ዋቢሸበሌ እና ገናሌዳዋ፣ የመካከለኛውና የታችኛው አፋርደናከል እና የታችኛው አዋሽ እንዲሁም በጥቂት የታችኛው ስምጥሸለቆ ተፋሰሶች በአብዛኛው ክፍል ላይ ከፊል ደረቅ እና ደረቅ ሁኔታ የተስተዋለ ሲሆን፡ በተቀሩት የተፋሰስ ቦታዎች ላይ መጠነኛ እርጥበት አግኝተዋል። በሌላ በኩል ከባድ ዝናብ የተመዘገበባቸው ተፋሰሶች ለውሃ ሀብት ግብዓት መጨመር ከፍተኛ አስተዋፆ ነበረዉ። ከዚህም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ በነበረው ከባድ ዝናብ ቅፅበታዊ ጎርፍና የወንዝ ሙላት አስከትሏል (ካርታ 5)።

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2017 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



## እ.ኤ.አ ከጁላይ 21-31/2017 የሚኖረው
## የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

ባለፉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ተጠናክረው ከመቆየታቸው ጋር ተያይዞ በብዙ አካባቢዎች ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ የነበረ ሲሆን በጥቂት ቦታዎች ላይም ነጎድጓዳማ የአየር ሁኔታ ለበረዶ አዘል ዝናብ ለመከሰቱ ምክንያት እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ።

በሚቀጥሉት አሥር አንድ ቀናት ወቅታዊው የክረምት ዝናብ በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖረውና ከዚህም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ከባድ ዝናብና አልፎ አልፎም በረዶ የቀላቀለ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል።

በዚህም መሰረት ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብና ሰሜን ሸዋ፣ የአርሲና ባሌ ዞኖች፣ ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፤ አዲስ አበባ፤ የጋምቤላ እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች፤ ከአማራ ክልል ምዕራብ እና ምሥራቅ ጎጃም፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ አዊ ዞን፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፤ የትግራይ ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የሀድያና የጉራጌ ዞኖች፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የወላይታ፣ የሲዳማ እና የጌዲዮ ዞኖች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በተለይም በምዕራብ አጋማሽ እና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ከባድ ዝናብ ሊከሰት ይችላል። ከዚህም ሌላ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፤ ከአፋር ክልል ደግሞ ዞን 3 እና ዞን 5፤ ከሶማሌ ክልል የጅግጅጋ እና የሲቲ ዞኖች እንዲሁም የድሬዳዋ እና ሐረሪ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ የደቡብ ኦሞ እና አጎራባች የሰገን ህዝቦች ዞኖች በአብዛኛው ደረቃማ የአየር ሁኔታ እያመዘነባቸው አነስተኛ ዝናብ ሊያገኙ ይችላሉ።

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 21-31/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻው
## ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የጁላይ ሦስተኛ አሥራ አንድ ቀናት የወቅቱ ዝናብ በተለያዩ የሀገሪቱ የክረምት ዝብ ተጠቃሚ ሥፍራዎች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖረው ከላይ የተጠቀሱ የትንበያ መረጀዎች ይጠቁማሉ። ይህም ሁኔታ በበልግ ዝናብ ተዘረቶ በተለየዩ የዕድገት ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ልዩልዩ የረጅም ጊዜ ሰብሎች እንደበቆሎ ፣ ማሽላ እና ዳጉሳ ላሉ፣ ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በክረምቱ ወቅት ቀደም ብሎ ለተዘሩ ለብርዕ ሰብሎች ማለትም

ጤፍ፣ ስንዴ ፣ ገብስ እና አጃ ላሉ ለጥራጥሬ ሰብሎች እንደ አተር፣ ባቄላ እና አደንጓሬ ለመሳሰሉት ሰብሎች በተጨማሪም ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ዉሃ አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል። በሌላ በኩል በአንዳንድ ሥፍራዎች አልፎ አልፎ በረዶ ቀላቅሎ እንደሚጥል የሚጠበቀዉ ከባድ ዝናብ ቅፅበታዊ ጎርፍ እንዲሁም በማሣ ላይ ዉሃ የመተኛት ችግር ሊያስከትል ስለሚችል ተጨማሪ ዉሃ ወደ ማሣ እንደይገባ ቦይ መቅደድና ዉሃዉን የማንጣፈፍ ሥራዎች መሰራት ተገቢ መሆኑን እንጠቁማለን ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች የሚጠበቀዉ የእርጥበት ሁኔታ በተለይም የመኸር አብቃይ አካባቢዎች ዋና የዘር ወቅት እንደመሆኑ መጠን አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ስለሆነ ከወዲሁ አስፈላጊዉን ቅድመ ዝግጅት ማድረጉ እና የተገኘዉን እርጥበት በአግባቡ መጠቀሙ ተገቢ መሆኑን እንመክራለን፡፡ አስቀድሞ የተሻለ እርጥበት በነበራቸውና የጥራጥሬ ሰብሎች ዘር መዝራት በተጠናቀቀባቸው አካባቢዎች በመብቀል እና በተለያዩ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች እንዲሁም በበልግ ወቅት ተዘርቶ በከፍተኛ የዉሃ ፍላጎት የዕድገት ደረጃ ላይ ለሆኑት የረጅም ጊዜ ሰብሎች የሚጠበቀው እርጥበት የተሻለ የውኃ አቅርቦት እንዲኖራቸው ስለሚያደርግ ለሰብሎቹ ጤናማ እድገት መልካም ሁኔታ የሚፈጥር ቢሆንም፡ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚጠበቀዉ ከባድ ዝናብ በተለያዩ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች በተለይም ሸክላማ አፈር፣ ዝቅተኛ እና ተዳፋት በሆኑት አከባቢዎች በማሣ ላይ ዉሃ የመተኛት ችግር እንዳይከሰት እንዲሁም ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊከሰት ስለሚችል ችግርን ለመቀነስ ተጨማሪ ዉሃ ወደ ማሣ እንዳይገባ ቦይ መቅደድና ዉሃዉን የማንጣፈፍ ሥራዎች መሰራት ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በተፈጥሮአቸዉ ዝናብ አጠር አካባቢዎች ላይ ዉሃ የማቆርና የመሰብሰብ ዘዴዎችን እንዲሁም የሚገኘዉን እርጥበት በአግባቡ እንዲጠቀሙ እንጠቁማለን፡፡

በሌላ በኩል ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸዉ የሚጠበቅባቸዉ አካባቢዎች መደበኛ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴዎች ማድረጉ ተገቢ ቢሆንም፡ በአንዳንድ በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ አጠር በሆኑ ቦታዎች ላይ የእርጥበት እጥረት ሊከሰት ስለሚችል የሚገኘዉን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን እንመክራል፡፡ በሌላ በኩል የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች በአብዛኛው ደረቃማ የአየር ሁኔታ በሚኖርባቸዉ የመኸር ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ በወቅቱ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረዉ ስለሚችል የሚገኘዉን እርጥበት በአግባቡ የመቆጠብና የመጠቀም ሥራዎች መሥራት ተገቢ መሆኑን እንጠቁማለን፡፡

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 21-31/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

# <u>አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

የክረምቱ ዝናብ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት ውስጥ በመጠንና በስርጭት ረገድ በተጠናከረ ሁኔታ የክረምት ዝናብ በሚያገኙት ተፋሰሶች ላይ ቀጣይነት እንዳለው ትንበያው ያመለክታል። ይህም ሁኔታ በአብዛኛው የአባይ፣ የተከዜ እና የባሮአኮቦ በተጨማሪም የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ አዋሽ፣ ስምጥሸለቆ እንዲሁም የላይኛው ገናሌዳዋ፣ ዋቢሸበሌና አፋርደናክል ተፋሰሶች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ የታችኛው አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆና ባሮአኮቦ እንዲሁም የመካከለኛው ዋቢሸበሌ ከመደበኛዉ ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። በሌላ በኩል የታችኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ገናሌዳዋ እና ዋቢሸበሌ በአብዛኛው ከፊል ደረቅ እና ደረቃማ ሁኔታ እንደሚያመዝናባቸው ይጠበቃል። በተለይ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የዝናብ ስርጭታቸው ከመደበኛው በላይ እና ከባድ ዝናብ የሚጠበቅባቸው ቦታዎች የወንዞች ሙላት እንዲሁም የጎርፍና የመሬት መንሸራተት ሊከሰት ስለሚችል ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል።